# ሳምንታዊ ዜና ዘገባ (ጥቅምት 1 ቀን 2001 ዓ. ም.)

**የሱማሌ ክልል ፕሬዝዳንትን ጨምሮ 10 የክልሉ ከፍተኛ ባለስልጣናት በመለስ ትዕዛዝ ከስልጣናቸው ተባረሩ፤ አብዱላሂ የሱፍ በአዲስ አበባ የቁም እስር ላይ ነው፤ ማባረሩ በግምገማ ተባለ እንጂ ከኦብነግ ጋር የተያያዘ መሆኑ ታወቀ፤ ወያኔ ግዙፍ ጦር በኦጋዴን ውስጥ አሰፈረ፤ የወያኔ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች ግምገማ ሊቀመጡ ነው፤ ወያኔ በህዝቡ ላይ ከፍተኛ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ አደረገ፤ ህዝቡ ለከፋ ችግር ተዳረገ፤ ለባለስልጣናቱ የቢሮና የሻይ አበል ተፈቀደላቸው፤ ለተሾመ ቶጋ እና ለሽታዬ ምናለ በውድ ዋጋ መኪና ተገዝቶ ተሰጣቸው፤ በእሬቻ በዓል ላይ መለስና አባዱላ ተወገዙ>>>>>>>>>>**

**ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ ሌላም ዜና በዝርዝር ያንብቡ ..........**

የወያኔ ቀንደኛ ካድሬ የነበረው የሱማሌ ክልል ፕሬዝዳንት አብዱላሂ የሱፍ ከሙስና ጋር በተያያዘ ነው ተብሎ ከስልጣኑ እንደተባረረ ታወቀ::

ባለፈው ሳምንት በይፋ የአብዱላሂ ዩሱፍ መነሳትን ተከትሎ በርካታ የክልሉ ባለስልጣናትም ተባርረው ለቁም እስረኛነት የተዳረጉ መሆኑን የገለፀው ከጅጅጋ የደረሰን ዘገባ በአሁኑ ሰዓት በጅጅጋና በሌሎችም የክልሉ ወረዳዎች ውስጥ መረጋጋት እንደሌለ ዘገባው አስረድቶዋል::

የወያኔ ቀኝ እጅ ነው እየተባለ በነመለስ ሲወደስ እና ሲሞካሽ የነበረው የሱማሌ ክልል ፕሬዝዳንት ከሙስና ጋር በተያያዘ ፓርቲው እንዳባረረው ቢገለፅም ሰውዬውን ያባረረው የወያኔው ሊቀመንበር መለስ ዜናዊ መሆኑን የገለፀው የደረሰን ዘገባ ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ ጊዜ ቤተ መንግስት ድረስ እያስጠራ ቢያስፈራራውም የመለስን ቁጣና ስድብ ከቁብ ባለመቁጠሩ የተነሳ ከኦጋዴን ብሔራዊ ነፃ አውጭ ግንባር መሪዎች ጋር ግንኙነት አለው ብሎ በመጠራጠሩ በሙስና አሳብቦ ከስልጣኑ ሊያባርረው እንደቻለ ይኸው የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል::

ከሌሎች የሱማሌ ክልል ፕሬዝደንቶች የተሻለ ለብዙ ጊዜ ስልጣን ላይ ቆየ የተባለው አብዱላሂ ቀድሞ በማስታወቂያ ሚኒስተር ውስጥ በጋዜጠኝነት ሲሰራ የነበረና እዛው እያለ የወያኔን ፖለቲካ ተጠምቆ አገልጋይ ካድሬ እንዲሆን ከተደረገ በሁዋላ ያለምንም ተወዳዳሪ በመለስ ዜናዊ ትዕዛዝ የሱማሌ ክልል ፕሬዝዳንት ሆኖ የተሾመ ሲሆን ፤በኦብነግ ላይ በሚወስደው ለዘብተኛ አቋዋም የተነሳ በመለስ ጥርስ ውስጥ እንደገባና ከስልጣን እንደተባረረ ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል::

በኦጋዴን ውስጥ በወያኔ ጦር ላይ ከፍተኛ ሰብዓዊና ቁሳዊ ጥቃት እየደረሰ ብዙ ጊዜ መለስ «ችግሩ ያንተ ደካማነት ነው :: በአካባቢው ያሉትን ነዋሪዎች እየሸነገልክ መያዝ ስትችል አልሰራህም» እያለ ቤተ መንግስት ድረስ እያስጠራ ሲሰድበው እንደነበረ የገለፀው ዘገባ መለስ በብስጭት «ከአሸባሪዎቹ ጋር ግንኙነት ሳይኖርህ አይቀርም »በማለት ኃይለ ቃል በመናገሩ አብዱላሂ ከናካተው ስራውን ትቶ በመኖሪያ ቤቱ ተወስኖ እንደነበርና እሱ ቤቱ በነበረበት ወቅትም ብዙ ችግሮች በክልሉ ውስጥ ተፈጥሮ እንደነበረም ዘገባው ገልፆዋል::

«የሱማሌን ክልል ልንቆጣጠረው ስላልቻልን አንተ ትይዝልናለህ እያልን ተስፋ ብናደርግም ከጥቅምህ ጉዳትህ ነው ያመዘነብን »በማለት የክልሉን ባለስልጣናት በሙሉ ቤተ መንግስት ድረስ አስጠርቶ ለ4 ሰዓታት የፈጀ ስድብና ዘለፋ ጭምር ሲያወርድባቸው የዋለ ቢሆንም የመለስን ቁጣና ስድብ ከምንም ሳይቆጥሩ ወደ ክልላቸው ተመልሰው በአብዱላሂ ዩሱፍ ሰብሳቢነት የግማሽ ቀን ስብሰባ የተካሄደ ሲሆን በዚሁ ስብሰባ ላይ « እኛ ለራሳችን የምናውቀው እኛ ነን እንጂ ማንም አይደለም» በማለት ለተሰብሳቢዎቹ በመግለፁ አዳራሹ በጭብጨባ ተናግቶ እንደነበር የገለጸው ዘገባው በወያኔ ደህንነቶች አማካኝነት ወሬው ለመለስ በመድረሱ እና በመናደዱ የሙስና ሰበብ አዘጋጅቶ ያባረረው መሆኑንም ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል::

እነ መለስ ዜናዊ በኦጋዴን ውስጥ በሚደርሰው ወታደራዊ ኪሳራ የተነሳ እየተበሳጩ አብዱላሂ ዩሱፍን «እኛ የሾምንህ እንድትሰራልን ነው እንጅ እንድትሰራብን አይደለም »እያለ ቤተ መብግስት ድረስ በተደጋጋሚ እያስጠራ ይሰድበውና ይቆጣው እንደነበረ የገለፀው የደረሰን ዘገባ በሚደርስበት ግልምጫና ስድብ ሁል ጊዜ እየተናደደ እና እየተበሳጨ ቢሮው ውስጥ ከሚገባበት የመይገባበት ቀናት ይበልጥ እንደነበረ ያስታወሰው ዘገባው በዚህም የተነሳ ስራውን መስራት ሁሉ አቁሞ እንደነበረም አብራርቶዋል::

በተለይም ከስድስት ወር ወዲህ በመለስ ንቀት እየተበሳጨና እየተናደዱ የነበሩት አብዱላሂና ካቢኔው ከመለስ የሚሰጣቸውን ትዕዛዝ ተግባራዊ ባለማድረጋቸው ልዩ የደህንነት አባሎች በስውር እንዲከታተሉዋቸው ጅጅጋ ተልከው እንደነበረም ዘገባው ጨምሮ አብራርቶዋል::

በአሁኑ ሰዓት ከፍተኛ ስጋት የሆነባቸው የሱማሌ ክልል እንደ አሁኑ ችግሩ አይባባስ እንጅ ከዚህ ቀደምም በነበሩት ስምንት ፕሬዝዳንቶች ጊዜ ተመሳሳይ ችግሮች ይስተዋሉ እንደነበረና የአሁኑ ግን በነመለስ ትልቅ ግምት ተሰጥቶት እንደፈለግነው እናሽከረክረዋለን ብለው እንዳሰቡት ሊሆንላቸው ባለመቻሉ የተቃዋሚነት ታፔላ ለጥፈው ከስልጣኑ አባርረው ለቁም እስረኛነት የዳረጉት መሆኑም ታውቁዋል::

የሱማሌ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ሶህዴፓ) ተብሎ በወያኔ የተቋቋቋመው ይኸው ድርጅት ምክትል ሊቀመንበሩን መሀመድ ድሪርን ከ8 ወር በፊት ከስልጣኑ አባርረው ተራ አባል እንዲሆን ያደረጉት ሲሆን፤ በዚህ ድርጊት የተበሳጨው መለስ አምባሳደር መሀመድ ድሪርን ወደ ነበረበት እንዲመልሱት በስውርም ሆነ በቀጥታ ትዕዛዝ ቢሰጣቸውም አንቀበልም በማለት በአቋዋማቸው የጸኑ መሆኑን የገለፀው ዘገባው በቅርቡ በሱማሌ ክልል ፕሬዝደንት እና ተከታዮቹ አቋዋም የተደናገጡት እነ መለስ የፌዴራል ባለስልጣናት እነ አባይ ፀሐዬ በተገኙበት በጅጅጋ ከተማ ውስጥም በተደረገ ግምገማ ላይ አብዱላሂ ዩሱፍ እንዲባረር ቢገፋፉዋቸውም አቋዋም ወስደው «አብዱላሂ እውነተኛ መሪያችን ነው» በማለት አስደንጋጭ መልስ በመስጠታቸው ክፉኛ የተቆጡት እነ አባይ ፀሐዬ ተመልሰው በጥቂት ቀናት ውስጥ በድጋሚ በተደረገ ስብሰባ ላይ ጥቂት የሱማሌ ክልል ተወላጆችንና የሱማሊኛ ቋዋንቋዋ ተናጋሪ የወያኔ የደህንነት ሰዎችን መልምለው አብዱላሂ ጥፋት አጥፍቶዋል ብላችሁ መስክሩና ከስልጣኑ ይነሳ በማለት በገንዘብ ጭምር ሙከራ ቢያደርጉም የአብዱላሂ ደጋፊዎች በመብዛ ቸው እንደበፊቱ ሳይሳካላቸው የቀረ ቢሆንም እነ አባይ ፀሐዬ ከመለስ የተሰጣቸውን ትዕዛዝ

ተግባራዊ ሳያደርጉ ቢመለሱ የሚጠብቃቸውን ስለሚያውቁ በማስፈራራት እንደ ታምራት ላይኔ አጥፍቻለሁ ስልጣኔን በገዛ ፈቃዴ ለቅቄያለሁ ብሎ በይፋ እንዲናገር በማድረግ ፖለቲካ ስራ ሰርተው ያወረዱት መሆኑንም ዘገባው አስረድቶዋል::

«በክልሉ የፖለቲካ አለመረጋጋት የተከሰተው በአግባቡ እና ፍትሀዊ በሆነ መልኩ የበጀት ክፍፍል ስለማይደረግ ከመሆኑም በተጨማሪ እኛን እንደ ሰው ስለማትቆጥሩን ነው » እያለ ፊት ለፊት ይጋፈጥ ነበር ያሉት ምንጮች በተለይም በክልሉ የልማት እንቅስቃሴ እየተዳከመ የሱማሌ ክልል በልማት እየመራ ነው ተብሎ መነገሩ እንደ ህፃን ልጅ ስለቆጠራችሁን ነው በማለት በቤተ መንግስት በተደረገው ምስጢራዊ ስብሰባ ላይ መናገሩ መለስን ያበሳጨው መሆኑን የገለፁት ምንጮች በኦጋዴን ውስጥ ህዝቡ በረሀብ እንደ ቅጠል እየረገፈ እያዩት የእርዳታ ድርጅቶች ገብተው ለህዝቡ የዕለት ጉርስ እንዳይሰጡ በመከልከላቸው የተነሳ ብዙ ህዝብና ከብቶች በተለይም ግመሎች መሞታቸውን ተከትሎ ይፋ ተቃውሞ በማሰማቱ « ይህች ጥሬ ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም » እንዲሉ ስለሆነባቸው ከስልጣኑ ሰበብ ፈልገው አባረረውት በአሁኑ ሰዓት በአዲስ አበባ ውስጥ በደህንነት ጥብቅ ቁጥጥር ስር እንደሚገኝም ገልፀዋል::

ከዚሁ ተባራሪ የወያኔ ባለስልጣን ጋር የተጠረጠሩ የክልሉ የቢሮ ኃላፊዎች በሙሉ ከስልጣናቸው ተባርረው በቁም እስረኛነት በጅጅጋ ከተማ ውስጥ እንዳሉና ሌሎችም ተመሳሳይ እጣ ሊገጥማቸው እንደሚችል ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሎዋል::

የወያኔ ቡድን የራሱን ጥቅም ከሌሎች ህዝቦች በላይ እያስቀደመ ለ17 ዓመታት ድረስ የመጣ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት ግን ይህንንኑ አቋዋሙን ይዞ ለመዝለቅ የሚያስችለው አይመስለኝም ያሉት አንድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህር በሱማሌ ክልል ውስጥ በደረሰው የሰብዓዊ ቀውስ አንድም ድጋፍ ሳያደርጉ ይባስ ብለው የእርዳታ ድርጅት ሰራተኞች የአቅማቸውን ያህል እንዳይረዱ ማባረራቸው የአካባቢው ህዝብ እንዲያልቅ ፅኑ ፍላጎት ያላቸው መሆኑን ያሳየ ስለሆነ እነ አብዱላሂ የሱፍ ከኦብነግ ጋር ግንኙነት አላቸው ቢባል ሊገርመን አይገባም ሲሉም ገልፀዋል::

የወያኔ ቀኝ እጅ እንደሆነና የመለስን ቃል እንደ ገደል ማሚቶ እያስተጋባ የነበረው አብዱላሂ በ1999 ዓ.ም. ግንቦት 20 በዓልን አስመልክቶ በጅጅጋ ከተማ ስታዲየም በማክበር ላይ እንዳለ በተጣለ ቦምብ ሰውነቱ እንደ ወንፊት ተበሳስቶ በሀገር ውስጥ ስለማይድን ተብሎ በውጭ ሀገር ታክሞ እንደመጣ የሚታወስ ነው::

በአሁኑ ሰዓት በሱማሌ ክልል ውስጥ የሚገኙ የዞንና የወረዳ አስተዳዳሪዎች እና የካቢኔ አባሎች ከያሉበት በሙሉ በጅጅጋ ከተማ ከትመው የሚገኙ በመሆኑ ወረዳዎቹንና የዞን ዋና ከተሞችን የሚያስተዳድረው ጠፍቶ የወያኔ የጦር አለቆች ከነጦራቸው ተበታትነው እያስተዳድሩ መሆኑንም ከተለያዩ ከተሞች የደረሱን ዘገባዎች አብራርተዋል::

ሳይጠሩዋቸው አቤት ሳይልኩዋቸው ወዴት እያሉ ወያኔን ሲያገለግሉት የነበሩት ባለስልጣናት በመለስ ዘንድ ታማኝነታቸው እየቀነሰ ሲመጣ እንደ አልባሌ ከስልጣናቸው እየተወረወሩ የሚጣሉ ሲሆን

በቅርቡ በሱማሌ ክልል ውስጥ የተጀመረው ሹም ሽረት በሌሎችም ክልሎችና በሚኒስትሮች ላይ ሊቀጥል ይችላል ሲል የደረሰን ዘገባ ጨምሮ አስረድቶዋል::

በአሁኑ ወቅት በሱማሌ ክልል ውስጥ አልሸባብ የተባለ አሸባሪ ቡድን እንቅስቃሴ ተጠናክሮ ቀጥሎዋል በሚል በለደወይን ተብላ በምትጠራው የሱማሌ ድንበር ላይ ሰፍሮ የነበረውን ግዙፍ ጦር በአካባቢው ወያኔ ያሰፈረ ከመሆኑም በተጨማሪ ከመሀል ሀገርም ወደ አካባቢው እያጉዋጉዋዘ መሆኑን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልፀዋል::

በሱማሌ ክልል በተፈጠረው ትርምስ በተለይም በኦጋዴን ፣በጎንደር እና በሞቃዲሾ በወያኔ ጦር ላይ እየደረሰ ያለው ከፍተኛ ኪሳራ እነመለስን ስላስደነገጠ በከፍተኛ መኮንኖቹ ላይ ለመለደፍ አስቸኩዋይ ግምገማ እንዲያደርጉና በማይፈልጉት መኮንን ላይ ሊያሳብቡ መዘጋጀታቸውን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋለጡ::

በሚቀጥለው ሳምንት ውስጥ ግምገማው ይጀመራል ተብሎ ይጠበቃል ያሉት ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ በሳሞራ የኑስና በታደሰ ወረደ ሰባሳቢነት በመኮንኖች አዳራሽ ውስጥ ምስጥራዊ ግምገማ እንደሚደረግም ምንጮቹ ገልፀዋል::

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሱማሌ ሞቃዲሾ ከተማና አካባቢዋ ፣በጎንደር፣ በኦጋዴን እና በሌሎችም የሀገሪቱ ክፍሎች ውስጥ ከመቸውም ጊዜ በላይ በወያኔ ላይ ከፍተኛ ወታደራዊ ኪሳራ እየደረሰበት በመሆኑ የተደናገጠው መለስ ዜናዊ በለመደው መንገድ ሀላፊነቱን ለማውረድና በመኮንንቹ ላይ ለማላከክ አስቸኩዋይ ግምገማ እንዲደረግ ጥብቅ ትዕዛዝ የሰጠ ሲሆን፣ ምናልባትም የአይናቸው ቀለም ያላማረ ከፍተኛ መኮንኖች የሚመነጠሩ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ የነመለስን ሀጢያት እንዲሸከሙ እንደሚደረግም ይጠበቃል ሲሉ ጨምረው ገልፀዋል::

ሱማሌ ክልል ውስጥ በተፈጠረው የፖለቲካ ቀውስ ሳቢያ የተቃዋሚ ኃይል ጥቃት ሊሰነዝር ይቻላል በሚል ስጋት የገባቸው የወያኔ የጦር መሪዎች ግዙፍ ጦር ወደ ስፍራው ያጉዋጉዋዙ ቢሆንም የውስጥ ችግር ስላለ ውጤታማ አንሆንም በሚል በቅርቡ የከፍተኛ መኮንኖች ግምገማ እንደሚደረግና ምናልባትም በተዋረድ እስከ ታችኛው የጦር አባል ድረስ ሊዘልቅ እንደሚችል ምንጮቹ ያላቸውን ግምት ሰንዝረዋል::

በቅርቡ አልሸባብ የተባለው የአሸባሪ ቡድን ተዋጊ ኃይልና ኦብነግ የተባለው የወያኔ ተቃዋሚ ኃይል በኦጋዴን በተለያዩ አካባቢዎች በሰነዘሩት ድንገተኛ ጥቃት በርካታ የወያኔ ወታደሮች ለሙትና ለቁስለኛ ነት የተዳረጉ ሲሆን ቁስለኞቹ ሐረር ከተማ ቀላድ አምባ አካባቢ በሚገኘው ወታደራዊ ሆስፒታል እና በአዲስ አበባ ቤላ ተብሎ በሚጠራው የማዕከላዊ ዕዝ ሆስፒታል ውስጥ ለህክምና መግባታቸውን የገለጸው የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ገለጻ ከዚህና ከመሳሰሉት ጋር ተዳምሮ የሱማሌ ክልል ፕሬዝዳንትና ባለስልጣናቱ ከኦብነግ መሪዎች ጋር ግንኙት አላቸው ተብሎ በነመለስ ስለታመነበት ለመባረርና ለቁም አስረኛነት እንደበቁም ምንጮቹ አስረድተዋል::

በአሁኑ  ሰዓት በኦጋዴን በርሀብ እየረገፉ ያሉት ወገኖች ቁጥር ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ ከመሆኑም ባሻገር የዕለት ጉርስ እንዳይደርሳቸው የእርዳታ ድርጅት ሰራተኞች ወደ ረሀብተኛው ወገን ጋር እንዳይሄዱ የወያኔ ወታደሮች እንቅፋት እየፈጠሩ መሆኑን የገለፁት የአለም አቀፉ ምግብ ድርጅት ሰራተኛ ብዙ የእርዳታ ድርጅቶች ወደ አካባቢው እንዳይሄዱ አሁንም ጫና እየተደረጋቸው መሆኑንም ሳይሸሽጉ ገልፀዋል::

በነሐሴ ወር መጨረሻ ላይ የሲ.ኤን. ኤን ቻናል ዘጋቢዎች እና የአልጀዚራ ጋዜጠኞች ወደ አካባቢው ይሄዳሉ ተብሎ በተሰማበት  ወቅት የወያኔ ወታደሮች በሄሊኮፕተር የሙዋች ሰዎችን አስከሬን እየለቃቀሙ በአንድ ጉድጉዋድ ውስጥ ከትተው ያቃጠሉት መሆኑን መዘገባችን የሚዘነጋ አይደለም::

በሀገሪቱ የኑሮ ውድነቱ እየተባባሰና ስር እየሰደደ ባለበት ወቅት ሰሞኑን በሚገርመም ሁኔታ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ መደረጉ ታወቀ::

በአንድ ሊትር እስከ 3ብር ድረስ ጭማሪ ያደረገው ወያኔ የህዝቡን አቅም ያላገናዘበ እና በህዝቡ መራብ መጠማት ቅንጣት ታክል ያልተቆረቆረ  በመሆኑ የተጋነነ በአለም ላይ ባልታየ ሁኔታ ጭማሪ በማድረግ ህዝቡን ከድጡ ወደ ማጡ  እየከተተው መሆኑም ታውቁዋል::

ቀድሞ 5ብር ከ72 ሳንቲም ሲሸጥ የነበረው የቤት ውስጥ መጠቀሚያ ነጭ ጋዝ ከ2 ብር ከ87 ሳንቲም በላይ እንዲጨምር ተደርጎ 8 ብር ከ 59 ሳንቲም በላይ እንዲያሻቅብ በመደረጉ በመላ ሀገሪቱ ያሉ ህዝቦች ለከፍተኛ የኑሮ ቀውስ መዳረጋቸው ተገልፆዋል::

ለወትሮው 6 ብር ከ90 ሳንቲም የነበረው የህዝብ ማመላለሻ መኪኖች የሚጠቀሙበት ነዳጅ 2 ብር ከ72 ሳንቲም ጨምሮ 9 ብር ከ92 ሳንቲም ያደገ ሲሆን በነዳጁ ዋጋ መጨመር ምክንያትም የትራንስፖርት ጭማሪው ከህዝቡ አቅም በላይ በመሆኑ ህዝቡ በእግር ለመጉዋዝ መገደዱም ታውቁዋል::

በተለይ የአዲስ አበባን ህዝብ ሲያገለግሉ የነበሩት የከተማ አንበሳ አውቶቡሶች ዋጋ በአንድ ጊዜ የ50 ሳንቲም ጭማሪ በማድረግ ተጠቃሚዎቹን ያማረረ ሲሆን ቀድሞ ዝቅተኛው አጭር ርቀት 50 ሳንቲም የነበረው በአሁኑ ጭማሪ አጭር ርቀት ጉዞ 1 ብር መሆኑን ድርጅቱ ከለጠፈው ማስታወቂያ ለመረዳት ተችሎዋል::

በቅርቡ ከቻይና የመጡት ቀንዶ ተብሎ በህዝቡ ዘንድ ስያሜ የተሰጣቸው 2 ብር ሲያስከፍሉ የነበረው አሁን በተደረገው ጭማሪ 2 ብር ከ40 ሳንቲም የገባ በመሆኑ ህዝቡ ለከፍተኛ ችግር መዳረጉን ተዘዋውሮ የተመለከተው ዘጋቢያችን ሪፖርት ያስረዳል::

የሚገርመውና የሚደንቀው የተደረገው የታሪፍ ጭማሪ ለሚኒባስ ታክሲዎች ላይ የ10 ሳንቲም ብቻ ሲሆን ይህም በቅርቡ በብድር የመጡት የቻይና ሰራሽ መኪኖች ብቻ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ እንዲሰሩ ለማድረግና ታክሲዎችን ከገበያ ውጭ ለማድረግ እቅድ መያዙን የሚያመለክት ነው ያሉት አንድ የታክሲ ባለንብረት ይህ ደግሞ ሊሆን የቻለው በ1997 ዓ. ም. በአዲስ አበባ ውስጥ ለ5 ቀናት

በተደረገው የስራ ማቆም አድማ ታክሲ ባለንብረቶች ተሳታፊ እንደነበሩና ስርዓቱን በግልጽ በመቃወማቸው ያ ችግር ዳግም እንዳይከሰት ለማድረግ መሆኑንም ባለንብረቱ በንዴት ገልፀዋል፡፡

የክፍለ ሀገር ሀገር አቋዋራጭ አውቶቡሶችም ላይ ከፍተኛ ጭማሪ የተደረገ ሲሆን በአንድ መከከለኛ የርቀት ተጉዋዦች 10 ብር ጭማሪ እንደተደረገባቸውም ለማወቅ ተችሎዋል፡፡በትራንስፖርቱ ላይ የተቆለለው የነዳጅ ጭማሪው በእህሉና በሸቀጦች ላይ ከሚጠበቀው በላይ እንዲቆለል ያደረገው በመሆኑ ህዝቡ ለከፋ ችግር ከመዳረጉ የተነሳ ብቻውን ለማውራት እየተገደደ መሆኑም ታውቋዋል፡፡

በዚያም አለ በዚህ ምን ጊዜም ተጠቃሚው የወያኔ ቱባ ባለስልጣኖች ናቸው ያሉት አንድ የጭነት ማመላለሻ ባለንብረት እነ በረከት ስምኦን ፤እነ ስዩነም መስፍን ፤ እነ አርከበ እቁባይ ፤ እነ አቦይ ስብሀት ፤ እነ አዜብ መስፍን በዘመዶቻቸው ስም በገዙዋቸው የደረቅና የፈሳሽ ከባድ መኪኖች ላይ ከፍተኛ ጭማሪ አድርገው አሁንም በተዘዋዋሪ መንገድ ህዝቡን እየመዘበሩት ነው ያሉት እኚሁ ባለንብረት ሌሎቻችንን ባለመኪናዎች ከውድድር ውጭ ለማድረግ በሞኖፖል ይዘውት እየተንቀሳቀሱ መሆናቸው አስገራሚ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

እንዲህ በህዝቡ ላይ በደልና ግፍ እየሰሩ ያሉት ባለስልጣናት እንደገና መልሰው የቢሮ አበል ፤ የሻይ ቡና አበል ፤የነዳጅ አበል እና የመሳሰሉት አበል እያሉ በቅርቡ ለራሳቸው ካደረጉት የደመወዝ ጭማሪ ሌላ ሰሞኑን አበሉ እንደተፈቀደላቸው ከተለያዩ መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች የደረሰን ጥቆማ ገለፀ፡፡ህዝቡ ላይ አንዴ የነዳጅ ጭማሪ ሌላ ጊዜ የቤትና የቦታ ግብር እያሉ እየቆለሉበት እንዳይናገርና እንዳይተነፍስ አድርገውት የእለት ጉርሱን እንኩዋን እንዳያገኝ የተለያዩ መሰናክሎች እየጋረጡበት እነሱ በአንፃሩ ግን ከህዝብ ላይ በዘረፉት ገንዘብ እንደልባቸው መንቀባረራቸው ሳያንስ በጀመሩት የንግድ ማዕከላት እንዳሻቸው ዋጋ በመጨመር ህዝቡ ላይ ጢቢ ጢቢ እየተጫወቱ መሆኑ ያሳዝናል ያሳፍራል ሲሉ የውስጥ አዋቂዎቹ በቁጭት ይገልፃሉ፡፡

ህዝቡ በርሀብና በኑሮ ውድነት እግር ከወርች ተጠፍንጎ የወያኔ ባለስልጣናት ግን እንደልባቸው በሀገርና በህዝብ ሀብት እየተንደላቀቁ በሀገሪቱ ረሀብ አልተከሰተም ቢከሰትም ከእኛ አቅም በላይ አይደለም እያሉ በረሀብተኛ ወገናችን ላይ መሳለቃቸው የአለምን ህዝብ ጭምር እያስገረመ ባለበት ወቅት ሰሞኑን ለባለስልጣናቱ አበል የሚያስፈቅድ ረቂቅ ቀርቦ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፀድቆ ለተወካዮች ምክር ቤት መቅረቡ ተገለፀ፡፡

በረቂቁ ላይ እንደሰፈረው ከሆነ የመንግስታዊ መስሪያ ቤቶች የመምሪያ ኃላፊዎችን ጨምሮ ሚኒስትሮችን የነዳጅ አበል ፤የቢሮ አበል፡ የሻይ ቡና አበል እና የሌሎችም ምክንያት ተጠቅሰው አበል በሚል ለዝቅተኛው ግልገል ባለስልጣን ሳይቀር ለየእያንዳንዱ ከ1500 ብር በላይ የተመደበላቸው ሲሆን ይህ ከሁለት ወር በፊት ለባለስልጣናቱ በደብዳቤ ከ300 ብር እስከ 500 ብር ድረስ ጭማሪ ከተደረገ በሁዋላ መሆኑንም ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

በህዝቡ ላይ የነዳጅ ዋጋ እንዲንር አድርገው ህዝቡ ቀድሞ በአንበሳ አውቶቡስ የሚሄድበት ታሪፍ እንኩዋን አሻቅቦ በእግሩ እንዲጉዋዝ አድርገው የወያኔ ባለስልጣናት ግን እንደልባቸው ከድሀው ህዝብ

ላይ በሚሰበስቡት ግብር እና በደሀው ህዝብ ስም በሚያገኙት ብድርና እርዳታ እየተምነሸነሹ ህዝቡን ረስተው ለብቻቸው እየኖሩ መሆኑ አሳዛኝና አሳፋሪ ነው ሲሉ አዲስ አበባ ነዋሪዎች በብስጭት እየገለፁ ናቸው::

የተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ተሽመ ቶጋ እና ምክትል አፈ ጉባኤዋ ወ/ሮ ሽታዬ ምናለ ከፋብሪካ የወጡ አዳዲስ የቶዮታ ምርት መኪኖች በውድ ዋጋ ተገዝተው እንደተሰጣቸው ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ዘገባ ገለፀ::

ሰሞኑን የ4ኛ ዓመት የስራ ዘመን ብለው በሚጠሩት ፓርላማ መክፈቻ ወቅት ለሁለቱ የወያኔ ቱባ ባለስልጣናት ለየእያንዳዳቸው ከ800 ሺህ ብር እስከ አንድ ሚሊዮን ብር የሚያወጡ መኪኖች ተገዝተው የተሰጣቸው መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ ህዝቡ በኑሮ ውድነትና በርሀብ እየተሰቃየ ባለበት በዚህ ወቅት ይህንን ያህል የህዝብ ገንዘብ ወጪ አድርገው የቅንጦት መኪና መገዛቱ አስገራሚና አስደናቂ ነው ሲሉ ምንጮቹ ገልጸዋል::

የወያኔ ባለስልጣናት በህዝብ ገንዘብና በሀገር ሀብት ያለ አንዳች ይሉኝታ እየተዝናኑበት ከመሆኑም ባሻገር ከራሳቸው አልፎ ለባዕዳን ጭምር የሀገሪቱዋን አንጡራ ሀብት እያግበሰበሱ እጅ መንሻ እያደረጉ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት በመላ ሀገሪቱ የከፋ የኑሮ ውድነት ሰፍኖ ባለበት ወቅት ደግሞ ህዝቡ በምግብ እጦት እየሞተ መሆኑን እያወቁ ለባለስልጣናቱ አበል መጨመር እና በውድ ዋጋ መኪኖችን መግዛት አሳፋሪና አሳዛኝ ተግባር ነው ሲሉ እነዚሁ የምክር ቤት ምንጮቻችን በንዴት ገልፀዋል::

በሌላ ዜና በየአመቱ የሚከበረው የእሬቻ በዓል ላይ ከ4 ሚሊዮን ህዝብ በላይ በመገኘቱ እነ መለስ ዜናዊን ማስደንገጡ የቤተ መንግስት ምንጮች ገለፁ:: ዘንድሮ ከመቸውም ጊዜ በላይ ቁጥሩ የበዛ ህዝብ በእሬቻ በዓል ላይ መገኘቱን የሰሙትና ተቀርፆ የመጣውን ፊልም የተመለከቱት መለስና የወያኔ ጀሌዎች እጅግ ከመደንገጣቸው የተነሳ በሀሳብ ተውጠው እንደነበር ምንጮቹ አጋልጠዋል::

በደብረዘይት ከተማ በየአመቱ የሚከበረው ሆራ አርሰዲ በዓል ላይ ወጣቱ የወያኔን መሪ መለስ ዜናዊን እና አባዱላ ገመዳን በኦሮሚኛ ቁወንቁዋ እያወገዙ በመሀል ደብረዘይት እየተመላለሱ ሲጨፍሩ እንደነበር የደረሰን ዘገባ ገልፆ ከዚህ ቀደም በየአመቱ በአዲሲ አመት መግቢያ መስከረም ወር የመጨረሻ እሁድ በደመቀ ሁኔታ የሚያከብሩ ቢሆንም ዘንድሮ ግን ህዝቡ እጅግ ብዙ ከመሆኑም በተጨማሪ ወጣቱ፤ ሴት ፤ወንድ ፤አዛውንት ሳይል በመለስ እና በወያኔ ላይ ብርቱ ታውሞ ሲያሰሙ እንደዋሉም ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል::

በከፍተኛ ሁኔታ የፌዴራል እና የክልሉ ፖሊስ ብርቱ ጥበቃ የተደረገበትና የደህንነት ኃይሎች እንደ አሸን በፈሉበት በዚሁ እሬቻ በዓል ላይ ወጣቱ ተቃውሞውን በይፋ እየገለፀ ባለበት ወቅት ጥቂት የተቃውሞ ቀስቃሽ ናቸው የተባሉ ወጣቶች በስውር ታፍነው ከመወሰዳቸው በስተቀር በተቃውሞ ተጀምሮ በተቃውሞ መጠናቀቁን የደረሰን ዘገባ አስታውቆዋል::

በተለይ የኦሮሞን ባህልና ወግ የማይከተለው የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳነት እና የኦህዴድ ሊቀ መንበር አባዱላ ገመዳ እንደ ማልድቦሮ ሲጋራ ማስታወቂያ ሰራተኛ ቡሽ ባርኔጣ አድርጎ ሙሉ ሱፉን ለብሶ የማዕከላዊ ኮሚተ ስብሰባ የተጠራ  መስሎ በመታየቱ ወጣቱ በጨኸትና  በፉጨት ተቃውሞ ያሰሙ ሲሆን አዛውንቶቹም ከፍተኛ ቅሬታ እንዳደረባቸው እና አባዱላም በህዝቡ እንቅስቃሴ በመደናገጥ በደህንነቶችና በአጃቢዎቹ ተከብቦ ከስፍራው እንደሸሸ የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል ፡፡